# የፌደራል ፍርድ ቤቶች የችሎት ስርዓት መመሪያ ቁጥር ----/2013

<u>የኮሚቴ አባላት</u>

ክብርት ወ/ሮ አሸነፈች አበበ

ክብርት ዳኛ ፀሀይ መንክር

ክብርት ዳኛ ሩታ ገ/ ፃዲቅ

ክቡር አቶ ዘሪሁን ጌታሁን

ክቡር ዳኛ ል**ዑለስላሴ ሊበን**

ክቡር ዳኛ እንዳለ ታደሰ

ክቡር አቶ ደበበ ኃ/ገብርኤል

**ጥር/201**

**3 ዓ.ም**

# የፌደራል ፍርድ ቤቶች የችሎት ስርዓት መመሪያ ቁጥር ----/2013

## መግቢያ

በኢፌዲሪ ህገመንግስት የዳኝነት ስልጣን ለፍርድ ቤቶች የተሰጠ ከፍተኛ ኃላፊነት በመሆኑ ይህንን ኃላፊነት በከፍተኛ ስነ ምግባር መፈፀም በማስፈለጉ፤

በፍርድ ቤቶች እስካሁን የችሎት ስርዓት መመሪያ ባለመኖሩ፣ ወጥነት እና ግልጽነት የጎደለው የችሎት ስርዓት አሰራር ሲከተሉ የነበረ በመሆኑ፣

ፍርድ ቤቶች የችሎቱን ስርዓት በጣሱት ላይ በዳኞች የሚሰጠው ቅጣት ወጥነት ያልነበረው በመሆኑ ወጥነት እንዲኖረው፣

የችሎት ስርዓት ለማክበርም ሆነ ለማስከበር በቅድሚያ መከበር የሚገባው የችሎት ስርዓት ምን እንደሆነ ዳኞች፣ ተከራካሪ ወገኖች፣ የችሎቱን ሂደት ለመከታተል ችሎት ላይ የተገኙ ሰዎች እንዲሁም ሌሎችም እንዲያውቁ እና እንዲመሩበት ማድረግ አስፈላጊ ስለሆነ፣

የፍርድ ቤቱ ማህበረሰብ እና ተገልጋዬች የችሎት ስርዓት አካሄድን እንዲያውቁ፣ የዳኝነት ስርዓት ተገማችነት ያለው እንዲሆን እንዲሁም የህብረ}ሰቡን አመኔታ ለማረጋገጥ፣

የፌደራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 27/2012 አንቀፅ 55(2) መሰረት የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይህን የፌደራል ፍርድ ቤቶች የችሎት

ስርዓት መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

**1** አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የፌደራል ፍርድ ቤቶች የችሎት ስርዓት መመሪያ ቁጥር ----/2013 " ተብሎ ሊጠራ ይችላል።

**2** ትርጓሜ

የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም ካላሰጠው በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

**1)** "ፍርድ ቤት" ማለት በፌደራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 27/2012 መሰረት የተቋቋመ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፣የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ማለት ነው።

**2)** **"ጉባኤ"** ማለት በፌደራል ዳኝነት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 26/2012 መሰረት የተቋቋመ የዳኞች አስተዳደር ጉባዔ ማለት ነው።

**3)** **"የፍርድ ቤት መሪ"** ማለት የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት ማለት ሲሆን የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ምክትል ፕሬዚዳንትንም ይጨምራል።

**4)** **"የፍርድ ቤት የበላይ አመራር"** ማለት የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኛ፣ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንቶችና ምክትል ፕሬዚዳንቶች ማለት ነው።

**5)** **"የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኛ"** ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የተሾመ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኛ ሲሆን፣ የፍርድ ቤቱን አመራሮችም ይጨምራል።

6) "ዳኛ" ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የተሾመ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት፣ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ዳኛ ነው።

7) “ምትክ ዳኛ” ማለት በፍርድ ቤት ትዕዛዝ የዳኝነት ወይም የሽምግልና ስልጣን ተሰጥቶት ስልጣን ያገኘበትን ጉዳይ በመመልከት ላይ ያለ ሰው ወይም ሰዎች ማለት ነው።

8) “የጉባኤው ተሿሚዎች” ማለት በፌደራል የዳኝነት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር26/2012 መሰረት በጉባኤ የሚሾም ነው።

9) "አስተዳደር ሠራተኛ" ማለት በፌደራል ፍርድ ቤቶች የአስተዳደር ሰራተኛ መተዳደሪያ ደንብ መሰረት የሚተዳደር ማንኛውም ሰራተኛ ማለት ነው።

10) “ችሎት” ማለት በፍርድ ቤት እውቅና ዳኛ ወይም ዳኞች ጉዳዮች የሚያከራክሩበት፣ ምስክሮች የሚሰሙበት እንዲሁም ውሳኔ የሚያነቡበት የችሎት አዳራሽ ክፍል ወይም ቦታ ማለት ነው።

11) “የችሎት ስነ ስርዓት አስከባሪ ፖሊስ” ማለት በፖሊስ ጣቢያ ወይም እንደ አስፈላጊነቱ ስልጣን ባለው አካል የችሎት ስርዓት እንዲያስከበር የተመደበ ፖሊስ ማለት ነው።

12) “የችሎት ስርዓት አስከባሪ ሰራተኛ” ማለት በፌደራል ፍርድ ቤቶች የአስተዳደር ሰራተኛ መተዳደሪያ ደንብ መሰረት የሚተዳደር በፍርድ ቤቱ የችሎት ስርዓት የሚያስከብር ሰራተኛ ማለት ነው።

13) “አቃቤ ህግ” በፌደራል ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ ማቋቋሚያ አዋጅ መሰረት አቃቤ ህግ ተብሎ የተሾመ ማለት ነው።

14) “ጠበቃ” ማለት የጥብቅና ሙያ አገልግሎት ለመስጠት ስልጣን ካለው አካል ፈቃድ ያገኘ የህግ ባለሙያ ሲሆን እንደ አስፈላጊነቱ የጥብቅና ፈቃድም ሳይኖረው የግል ድርጅቶች፣ የልማት ድርጅቶች እንዲሁም ሌሎች የመንግስት መስሪያ ቤቶቹን ወክሎ የሚከራከር ነገረፈጅ ሆኖ የመከላከያና የፌደራል ፖሊስ ነገረፈጅ እንዲሁም ተከላካይ ጠበቆችንም ይጨምራል።

15) “አስተርጓሚ” ማለት የፌደራል የስራ ቋንቋ መናገር ወይም መረዳት ለማይችሉ ባለጉዳዮች የቋንቋ ትርጉም አገልግሎት የሚሰጥ ሰው ሆኖ የምልክት ቋንቋ የሚያስተረጉም ሰውንም ይጨምራል።

**16)** “ባለ ጉዳዮች” ማለት እየተካሄደ ባለ ክርክር ውስጥ የሚሳተፉ እንደ ከሳሽ፣ ተከሳሽ፣ አመልካች፣ዐቃቤ ህግ፣ ጠበቃ፣አቤቱታ አቅራቢ፣ ተጠሪ፣ የክርክር ጣልቃ ገቦች፣ ውሳኔ ለመቃወም ወደ ክርክር የገቡ ወይም የይግባኝ ባይ እና የመልስ ሰጪ ሆነው ችሎት ላይ የቀረቡ ወይም ማንኛውም የፍርድ ቤቱ ተገልጋይ ወይም ታዳሚ ማለት ነው፡፡

**17)** “ምስክር” ማለት በክስ ወይም መልስ ላይ የተዘረዘረ ወይም በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ችሎት ላይ ቀርቦ የምስክርነት ቃሉን የሚሰጥ ምስክር ሆኖ የባለሙያ ምስክርን ይጨምራል፡፡

**18)** “ፖሊስ” ማለት የፍርድ ቤትን ትዕዛዝ ለመፈጸም ችሎት ላይ የሚቀርብ ፖሊስ ሲሆን ይኸውም መደበኛ ፖሊስ፣ የማረሚያ ቤት ፖሊስ፣ የክልል ፖሊስ፣ ፌደራል ፖሊስ፣የጉምሩክ መስሪያ ቤት ፖሊስ እና ትራፊክ ፖሊስን ይጨምራል፡፡

**3.** የጾታ አገላለፅ

በዚህ መመሪያ ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለፀው አነጋገር የሴት ፆታንም ያካትታል፡፡ **4.**ዓላማ

ይህ መመሪያ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፡-

1. የፍርድ ቤቶች ችሎቶችን ስርዓት ማረጋገጥ
2. ወጥነት እና ግልጽነት ያለው የችሎት ስርዓት ማረጋገጥ
3. የችሎት ስርዓትን ዳኞች፣ ተከራካሪ ወገኖች፣ የችሎቱን ሂደት ለመከታተል ችሎት ላይ የተገኙ ሰዎች እና ሌሎችም እንዲያውቁ እና እንዲመሩበት ለማድረግ እንዲሁም የህብረሰቡን አመኔታ ማረጋገጥ፣

**5.** የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በፌደራል ፍርድ ቤቶች ችሎት ሂደት ሁሉ ላይ በችሎት ሂደት ውስጥ በሚሳተፍ ማንኛውም ሰው በተለይ ዳኛ፣ የጉባኤ ተሿሚ፣ ተከራካሪ ወገኖች፣ ምስክሮች፣ አስተርጓሚ፣ የፍርድ ቤቱ አስተዳደር ሰራተኞች፣ የችሎት ስነ ስርዓት አስከባሪ ፖሊስ፣ የፍርድ ቤቱ ችሎት ስነ ስርዓት ሰራተኛ ፣ የችሎት ታዳሚዎች፣ ፖሊሶች፣ ምትክ ዳኛ፣ አቃቢያን ህግ፣ ጠበቆች ወይም ከችሎት ውጪ በፍርድ ቤቱ ቅጥር ግቢ በሚገኝ ማንኛውም ሰው ላይ ተፈጻሚነት ይኖረዋል፡፡

ክፍል ሁለት

ቅድመ ችሎት ስርዓት

**6.** የቅድመ ችሎት ስርዓት

1) ችሎት ከመጀመሩ በፊት የችሎት ውሎ ፕሮግራምን የሚያመላክት እንዲሁም በእለቱ የተቀጠረ መዝገብ ቁጥር፣ የተቀጠረበት ሰዓት፣ የባለ ጉዳዮችን ስም፣ የጉዳዩን አይነት እና ጉዳዩ የተቀጠረበት ምክንያት የሚያመለክት የማስታወቂያ ሰሌዳ በግልጽ ቦታ መለጠፍ አለበት፡፡

2) ከችሎት ከመጀመር በፊት ጉዳዩ የሚመለከታቸው የፍርድ ቤት ሰራተኞች በሙሉ ችሎቱ ስለመፀዳቱ ማረጋገጥ፣ በችሎት አዳራሽ መብራት፣ የእለቱ መዝገብ ፣የዳኛ አጀንዳ፣የዳኞች ስም ያለበት የጠረጴዛ ባጅ፣ ህጎች፣ የችሎት ወረቀት፣ ብዕር፣ የድምጽ መቅረጫ፣ ችሎት መዶሻ፣የዳኛ ስም እንዲሁም በችሎት መሟላት ያለባቸው በሙሉ ስለመሰናዳታቸው ማረጋገጥ አለበት፡፡

3) አቃቢያን ህጎች፣ ጠበቆች፣ ባለ ጉዳዮች፣ በወንጀል የተጠረጠሩ ወይም የተከሰሱ ሰዎች እንዲሁም ሌሎች ሰዎች ችሎቱ ከመጀመሩ በፊት ወደ ችሎቱ አዳራሽ ወይም ክፍል ገብተው የተዘጋጀላቸውን ቦታ መያዝ አለባቸው፡፡

4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ሁለት እና ሶስት ስር የተደነገገው ስርዓት ከተፈጸመ በኋላ የችሎት ስርዓት አስከባሪው ወይም ፖሊስ በችሎቱ አዳራሽ ውስጥ የተገኙት ሰዎች በሙሉ ዳኞች ወደ ችሎት ሲገቡ ተነስተው እንዲቀበሏቸው በማሳሰብ ዳኞች የሚዘጋጁበት ክፍል በመሄድ ከእነርሱ ቀድመው ችሎት በማስገባት፣ የመቀመጫቸው ቦታ ሲደርሱ ለዳኞች ወታደራዊ ሰላምታ

በምልክት በመስጠት ከዚያም ችሎት ውስጥ ወዳሉት ሰዎች በመዞር እነርሱንም በምልክት ሰላምታ ጠይቆ እንዲቀመጡ ያደርጋል።

**7** የችሎት አጀማመር ስርዓትና ሰዓት

1. የተለየ ሁኔታ ካልተፈጠረ በስተቀር የፍርድ ቤት ችሎት ጠዋት በ3፡00 እና ከሰዓት በ8፡00 መጀመር አለበት።የአየር ሁኔታ ፀባይ በተለየ ሊታዩ የሚገባቸው እንደ ክልሉ ነባራዊ ሁኔታ ሊቀያየር ይችላል።
2. በችሎት መዶሻ በመምታት ችሎቱ ይጀመራል።

8. ባለ ጉዳዮች የሚስተናግዱባቸው ቅደም ተከተል

1) ችሎቱ የሚቀርቡለትን ጉዳዮች በሚከተለው ቅደም ተከተል ማስተናገድ አለበት። ሀ) ፍርድ፣ ቅጣት፣ ውሳኔ፣ ብይን ማንበብ ወይም መንገር

ለ) ትዕዛዝ ማንበብ ወይም መንገር

ሐ) መልስ፣ የጽሁፍ ማስረጃ፣ አስተያየት መቀበል

መ) የእምነት ክህደት ቃል መቀበል ወይም የሚካሄደውን የቃል ክርክር ማድመጥ

ሠ) ምስክሮች መስማት

ረ) በእለቱ በተስተናገደው መዝገብ ላይ አቤቱታ ከባለጉዳይ ሲቀርብና ዳኛው የቀረበውን ምክንያት ሲቀበል

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ስር የተደነገገው ቢኖርም ዳኛው እንደ አስፈላጊነቱ ፣ ለታማሚ፣ ለአካል ጉዳተኛ፣ ለነፍሰጡር ሴቶች፣ ህጻናት ለያዙ፣ ለእስረኛ ለመሳሰሉት ሰዎች ቅድሚያ መስጠት ይችላል።

9. የቃለ መሐላ ስርዓት

1) ቃለ መሀላ ፍትህን እና እውነትን በማውጣት ረገድ ከፍተኛ ድርሻ ስላለው በህጉ አግባብ የመማል ግዴታ ያለበት ማንኛውም ሰው፣ተከራካሪዎች፣ አስተርጓሚን ጨምሮ ባህል፣ ሐይማኖት እና ወጉን ሊገልጽ በሚችል እና እውነት ለመናገር ሊገደድ በሚችል አግባብ መማል አለበት።
2) ቃለ መሀላ በዳኛ ፊት ሆኖ መሀላው በዳኛ ወይም በፍርድ ቤቱ አስተዳደር ሰራተኛ የሚፈጸም ሆኖ ቃለ መሀላ የሚፈፅሙ ሰዎች በግልፅ ለችሎቱ ሊሰማ በሚችል ለየብቻ ቃለ መሀላ መፈፀም አለባቸው።
3) ማንኛውም ሰው በባህሉ ወይም በሐይማኖቱ መሰረት መጽሐፍ ቅዱስ ወይም ቁርዓን ይዞ መማል ወይም ቀኝ እጁን ከፍ በማድረግ ቃለ መሀላ መፈፀም አለበት።
4) ዳኛው ወይም የፍርድ ቤቱ አስተዳደር ሰራተኛ ሰዎችን ቃለ መሀላ ከማስፈፀሙ በፊት የሚምለው ሰው በምን እንደሚያምን፣ የመሀላውን ዓላማ እና ውጤት በማስረዳት ቀጥሎ በተገለፀው መልኩ በዝርዝር በአግባቡ ቃለ መሀላ ማስፈፀም አለበት።

«በዚህ ፍ/ቤት ፊት ቀርቤ በእውነት ለመመስከር/ ለማስተርጎም /ለመናገር በፈጣሪ /በአምላክ /በእግዚአብሄር /በአላህ ስም

እምላለሁ። በዚህ ፍ/ቤት ፊት ቀርቤ እውነት እንጂ ሃሰት ብናገር ፈጣሪ /አምላክ/እግዚአብሔር/አላህ ይፍረድብኝ።»

10. ችሎት ፊት ስለመቆም/ለችሎት ክብር ስለመቆም

1) በችሎት ሂደት ፍርድ ቅጣት ውሳኔ ብይን ሲነበብ፣ የክስ እና መልስ ቅብብል ሲደርግ፣ ክርክር ሲካሄድ፣ ባለጉዳዩ ምስክሮችን ሲያሰማ፣ አቤቱታ ሲያቀርብ፣ ትዕዛዝ ሲሰጥ፣ ውሳኔ ሲነበብ ወይም ዳኛው በያዘው ጉዳይ በሚያስችልበት ወቅት የሚመለከተው ባለጉዳይ ቆሞ መከታተል አለበት፡፡
2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ስር የተደነገገው ቢኖርም ችሎቱ እንደየሁኔታው ክርክሩ የሚራዘም ከሆነ አንደኛው ወገን ሲናገር ሌላኛው ወገን እስከዚያ ድረስ እንዲቀመጥ፣ በጋራ ከተከሰሱት ወይም ከከሰሱት ሰዎች መካከል ምስክር ከሚያሰማ ወይም ከሚሰማበት ውጪ ያለው ተከሳሽ ወይም ከሳሽ እንዲቀመጥ እንዲሁም በህመም ወይም እርግዝና ወይም አካል ጉዳት ምክንያት መቆም የማይችል ሰው እንዲቀመጥ ዳኛው ሊፈቅድ ይችላል፡፡

11. ድምፅን ከፍ አድርጎ ስለመናገር

1) ዳኛ ችሎት ሲመራ ለችሎት ታዳሚዎች በሙሉ በሚሰማ መልኩ መናገር አለበት፡፡
2) አቃቢያነ ህግ፣ ጠበቆች፣ ምስክሮች እና ባለ ጉዳዮች ክርክራቸውን ሲያቀርቡ ችሎቱ እና ተከራካሪው ወገን ሊሰማ በሚችል ሁኔታ መናገር አለባቸው፡፡

12. የአለባበስ ስርዓት

1) ማንኛውም ዳኛ ችሎት ሲያስችል ሙሉ ጥቁር የሆነ ጋወን/ካባ መልበስ አለበት።

2) እንደ ችሎቱ ባህርይ (የቤተሰብ፣ የሕፃናት፣ የወጣቶች) ዳኞች፣የሕግ ባለሙያዎች እንዲሁም ችሎት አስከባሪዎች በችሎት ካባ ለመልበስ እንዳይገደዱ ፍርድ ቤቱ ሊፈቅድ ይችላል።

3) በችሎት የሚገኝ አቃቤ ህግ ሙሉ ጥቁር ካባ አንገቱ ላይ ቀይ የሆነ፣ ጠበቃ ሙሉ ጥቁር ካባ፣ እና ተከላካይ ጠበቃ ሙሉ ጥቁር ካባ አንገቱ ላይ አረንጓዴ የሆነ መልበስ አለበት።

4) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 እና 3 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም ዳኛ፣ ዐቃቤህግ፣ ጠበቃ ከካባው ውስጥ ለወንድ ሱፍ/የጨርቅ ኮትና ሱሪ፣ ሸሚዝ፣ ከረባት ለሴት ሱፍ/የጨርቅ ኮትና ሱሪ ወይም ቀሚስ ፣ ሸሚዝ ወይም ሹራብ መልበስ እና ካባው

እስከ አንገት ድረስ በቁልፍ ወይም በዚፕ የተዘጋ መሆን አለበት።

5) ማንኛውም ዳኛ ወይም ረዳት ዳኛ ለወንድ የተፈረዘ ወይም ያደገ ፀጉር ለሴት አንፀባራቂ ቀለም የተቀባ ፀጉር፣ እይታን የሚከለክል የፀጉር አሰራር፣ አንፀባራቂ ጌጣጌጥ ማድረግ የለበትም/የለባትም።

6) ረዳት ዳኞች፣ የግል ድርጅት፣ የመንግስት የልማት ደርጅቶች እና የመሳሰሉት ወክለው የሚከራከሩ ተወካዮች/ጠበቆች ወይም ነገረፈጆች

ላይ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 ድንጋጌዎች ተፈጻሚነት አይኖረውም። ሆኖም ለወንድ ሱፍ/የጨርቅ ኮትና ሱሪ፣ ሸሚዝ፣ ከረባት

ለሴት ሱፍ/የጨርቅ ኮትና ሱሪ ወይም ቀሚስ ፣ ሸሚዝ ወይም ሹራብ መልበስ አለባቸው።

7) የችሎት አስከባሪ ፖሊስ ለዚህ ስርዓት የሚውል የደንብ ልብስ መልበስ አለበት።

8) ሬጅስትራር ፣ የችሎት ስነስርዓት አስከባሪ፣ ድምፅ ቀራጭ እንዲሁም በችሎት መገኘት ያለባቸው የፍርድ ቤቱ ሰራተኞች የችሎቱን ክብር የሚመጥን በፍርድ ቤቱ ህጋዊ እውቅና ያገኘና በፍርድ ቤቱ ወጪ የተዘጋጀ የደንብ ልብስ ወይም ካባ መልበስ አለባቸው።

9) የፍርድ ቤቱ አስተዳደር ሰራተኞችም ሆኑ የችሎት ታዳሚዎች የተለየ የአለባበስ ሰርዓት እንዲከተሉ አይገደዱም። ሆኖም የችሎቱን ወይም የፍርድ ቤቱን ክብር የሚያቀል ወይም የችሎቱን ስራ የሚያደናቅፍ ድብቅ የሰውነት ክፍልን የሚያሳዩ ወይም ውስጥ የሰውነት ክፍልን

የሚያሳዩ ወይም በጣም አጫጭር የሆኑ ቀሚሶች (Miniskirt) ሱሪዎች ወይም ጥብቆዎች ለብሰው ችሎት መግባት የተከለከለ

ነው።የወንጀል ድርጊትን የሚቀሰቅሱ ወይም በዳኝነት ሂደቱ ላይ ተጽዕኖ ሊያሳርፉ የሚችሉ ጽሁፎች ወይም መፈክሮች ያሉባቸውን ልብሶች ለብሰው በችሎት እንዲታደሙ አይፈቀድም።

10) ማንኛውም ሰው በሐኪም ካልታዘዘለት በቀር አይኑ እንዳይታይ የሚያደርግ ወይም ጥቁር መነጽር አድርጎ ችሎት መግባት የለበትም። 11) ዳኛ፣ አቃቤ ህግ እና ጠበቃን ጨምሮ ማንኛውም ሰው ማንነቱን ሊደብቅ የሚችል ኮፍያ ወይም ጥምጣም በጭንቅላት ላይ ጠምጥሞ ችሎት መግባት የለበትም።

12) ማንኛውም ሰው ፊት እና አይኑን ሙሉ ለሙሉ የሚሸፍን ወይም ሰው እንዳያየው የሚያደርግ ልብስ ለብሶ ችሎት መግባት የለበትም። 13) በዚህ አንቀጽ የተደነገገው ቢኖርም በሐይማኖት ወይም በባህል ምክንያት የሚለበሱ ልብሶችን ለብሶ ችሎት መግባት ይቻላል። ሆኖም ችሎቱ የዚህን ሰው ማንነት ለማጣራት ወይም ለማረጋገጥ ሲል የዚያን ሰው ክብር፣ ባህል እና ሐይማኖት በማይጋፋ መልኩ ልብሱን ከላዩ ላይ እንዲያነሳ ማዘዝ ይችላል።

14) ማንኛውም ጠበቃ ወይም አቃቢያን ህግ ከችሎት ውጪ ጋወን/ካባ በአግባቡ ለብሶ ወደ ችሎት መግባት አለበት፤ችሎት ላይ ጋዎን/ካባ ማውለቅ እና መቀያየር የለበትም።

15) ማንኛውም ሰው የችሎትን ፀጥታ በድምፅ የሚያውክ ጫማ በችሎት ወይም በዳኞች ቢሮ/ፅ/ቤት አካባቢ ማድረግ የለበትም። 16) የተጨማደደና ንጽሕናውን ያልጠበቀ ካባ ለብሶ ወደ ችሎት መግባት የተከለከለ ነው።

**13.** ተንቀሳቃሽ ስልኮች ወይም በድምጽ ሊያውኩ የሚችሉ ሌሎች ኤሌክትሮኒክስ መሣሪያዎች

ማንኛውም የችሎት ታዳሚ ወይም ባለጉዳይ ተንቀሳቃሽ ስልኮችን ወይም በድምጽ ሊያውኩ የሚችሉ ሌሎች ኤሌክትሮኒክስ መሣሪያዎችን ወደ ችሎት ከመግባቱ በፊት ድምፅ እንዲያጠፋ ይገደዳል፡፡

**14** ችሎቱን ስለማክበር

ማንኛውም የፍርድ ቤቱ ሰራተኛ፣ፖሊስ ፣ የችሎቱ ተገልጋይ፣ ተከራካሪ ወይም ባለጉዳይ በሚከተሉት ሁኔታዎች እራሱን ዝቅ በማድረግ ለችሎቱ ያለውን ክብር ሊያሳይ ይገባል፤

1. ዳኛው ወደ ችሎት ሲገባና ሲወጣ
2. ዳኛ በተሰየመበት ችሎት ወደ ችሎቱ ሲገባና ሲወጣ
3. ማንኛውም ባለጉዳይ በችሎቱ አቋም ባይስማማም ችሎቱ ትዕዛዝ፣ ብይን፣ ፍርድና ውሳኔ አንብቦ ሲጨርስ
4. ችሎት ትዕዛዝ፣ ብይን፣ ፍርድና ውሳኔ አንብቦ ከጨረሰ በኋላ በጉዳዩ ላይ ክርክር ማንሳት ወይም ስሜታዊ በሆነ ሁኔታ አቋምን መግለጽ የተከለከለ ነው
5. ዳኞች ችሎት ሲሰየሙና ሲወጡ ራሳቸውን ዝቅ በማድረግ ታዳሚውን እጅ ይነሳሉ፡፡

15 የዳኞች መጠሪያ ስያሜ

1. የፍርድ ቤቱ መሪ እንዲሁም የበላይ አመራሩ በማንኛውም ወቅት እንደ ቅደም ተከተላቸው የክብር ስማቸውን ለሴት #ክብርት$ ለወንድ #ክቡር$፣ ኃላፊነታቸውና ሙሉ ስማቸው በመግለፅ ተገቢውን ክብር በመስጠት ንግግር ሊደረግ ይገባል፡፡

2. ማንኛውም ሰው በችሎት ውስጥ ወይም ከችሎት ውጪ በማንኛውም ለጠቅላይ ፍ/ቤት ዳኞች #**Justice**$ ፣ ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና ለፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ለሴት ዳኛ #ክብርት ዳኛ$ እንዲሁም ለወንድ ዳኛ #የተከበሩ ዳኛ$ በማለት መጥራት አለባቸው፡፡

16 በግልጽ ችሎት ስለመዳኘት

1) በዝግ ችሎት እንዲታዩ በህግ ከተደነገጉት ውጪ ማንኛውም ጉዳይ
በግልጽ ችሎት መካሄድ አለበት፡፡

2) ማንኛውም ሰው ችሎት ገብቶ የችሎቱን ሂደት የመከታተል መብት አለው፡፡

17 የቀጠሮ አሰጣጥ ስርዓት

1) ማንኛውም ዳኛ በጉዳዬች ፍሰት አስተዳደር ለጉዳዩ በተቀመጠው ጊዜ መሰረት መዛግብትን መቅጠርና ማስተናገድ አለበት፡፡

2) ዳኛ ቀጠሮ የሚሰጠው የስራ ብዛት፣ የጉዳዩን ባህሪ እና ክብደት እንዲሁም የባለ ጉዳዮችን ችግር ከግምት ባስገባ መልኩ ይሆናል፡፡

3) ማንኛውም ዳኛ መዝገብ ሲቀጥር ጉዳዩ የሚታይበትን ሰዓት፣ ቀን እና ወር እንዲሁም ችሎት ለይቶ መግለጽ አለበት፡፡ መዝገቡ እልባት ካልተሰጠው ወይም ካልተቋጨ በስተቀር በመዝገቡ ላይ ቀጣዩ ሂደት፣ ሂደቱ የሚከናወንበትን ቀንና ጊዜ ለባለጉዳይ ማሳወቅና በመዝገቡ ላይ ማስፈር አለበት፡፡

**18** ከዳኞች የሚጠበቅ ስርዓት

1) የችሎቱ የእለት መዝገብ መዘጋጀቱ፣ ባለጉዳዮች መዘጋጀታቸውን ማረጋገጥ፣ መዛግብትን እንደ ቅደም ተከተሉ መለየት 2) የስራ ሰዓትን አክብሮ ችሎቱን መምራት፣ በበቂ ምክንያት ካረፈዱ ባለ ጉዳዮችን በማክበር ይቅርታ መጠየቅ፤

3) የችሎቱ ሰብሳቢ ዳኛ ወይም ዳኛ ጠረጴዛውን በችሎት መዶሻ በመምታት ችሎቱ ስለመጀመሩ ማብሰር አለበት፡፡

4) ዳኞች በፍርድ ቤቱ አስተዳደር በሚወጣ የችሎት ፕሮግራም

መሰረት በግልፅ ችሎት ማስቻል 5) ዳኛ ችሎቱን ሲመራ

የህዝቡን ባህል፣ ወግ እና ሐይማኖት በማክበር መምራት፤

6) ለተከራካሪዎች ለፍርድ ቤቱ አስተዳደር ሰራተኞች፣ ፣ፖሊሶች፣ ለተለያዩ መ/ቤቶች ተወካዮች፣ የችሎት ታዳሚዎችን ወይ

7) ተከራካሪ ወገኖችን፣ ምስክሮችን እና ሌሎች ችሎቱን የሚከታተሉ ሰዎችን አክብሮትን በሚያሳይ መልኩ የሙያ ማእረግ በመጠቀም፣አቶ ወይም ወ/ሮ፣ወ/ሪት ወይም እርስዎ በሚሉት ቃላት መጥራት፤

8) በቀጠሮ እለት ውሳኔ ወይም ትዕዛዝ ካልደረሰ ምክንያቱን ለባለ ጉደዮች በመግለጽ ይህንኑ በመዝገብ ላይ በመመዝገብ ጉድለቱ የፍርድ ቤት ወይም የችሎቱ ወይም የዳኛው ከሆነ ይህንኑ ለባለ ጉዳዩ በመግለጽ በትህትና ይቅርታ መጠየቅ፤

9) ማንኛውም ዳኛ የዳኝነት ፍትሀዊ አካሄድ መርህ በተላበሰ ማንኛውም ባለጉዳይ ሳያሸማቅቅ ሀሳቡን በነጻነት እንዲገልፅ ማድረግ፤ 10) ዳኞች መዝገቦችን በተቀጠሩበት ቀንና

ሰዓት ያለመዘግየት ማስተናገድ

11) የችሎቱን ስነ ስርዓት ማክበርና ማስከበር፣

12) የችሎቱ ሰብሳቢ ዳኛ ወይም ዳኛው ስራውን ከመጀመሩ በፊት ባለ ጉዳዮችን እና ችሎት ለመከታተል የተገኙ የችሎት ታዳሚዎች በሙሉ ሰላምታ በመጠየቅ "ባለ ጉዳዮች እና ችሎት ለመከታተል የመጣችሁ ሰዎች በሙሉ እንኳን ደህና መጣችሁ" በማለት ማንነቱን

አስተዋውቆ፣ በሶስት ወይም ከዚያ በላይ ዳኞች የተሰየመ ችሎት ከሆነ ደግሞ ሁሉንም ዳኞች እንደ አሰያየማቸው በቅደም ተከተል ማንነታቸውን ማስተዋወቅ አለበት።

19. ከባለጉዳዮቹ የሚጠበቅ ስነምግባር

1 በቀጠሮው ቀን፣ ቦታና ሰዓት መገኘት አለበት፤

2 በቀጠሮ ቀን ለክርክሩ በአግባቡ ተዘጋጅቶ መቅረብ አለበት፣

3 ዳኞች በችሎቱ ሲኖሩም ሆነ በማይኖሩበት ጊዜ በችሎቱ ክፍል ወይም አዳራሽ ውስጥ የችሎቱን ስነ-ምግባር ለማስጠበቅ በችሎቱ የሚሰጠውን የማስከበሪያ ትዕዛዝ ማክበር አለበት፤

4 በችሎቱ ላይ ተራቸውን በመጠበቅ ክርክር ማቅረብ፤

4) የፍርድ ቤቱ ባለጉዳዮች የሚጠይቁትን ዳኝነት በህጉ አግባብ የፍርድ ቤቱን ሂደት እና አሰራር በማክበር መፈጸም

5) በችሎቱ ዳኛ ክስ እየተነበበ፣ ቅጣት ውሳኔ ብይን ወይም ፍርድ እየተነበበ ወይም ምስክር እየተሰማ ሳለ ማንኛውም ሰው ችሎት አቋርጦ መውጣት የለበትም

6) ያቀረቡትን ክርክር፣ ተቃውሞ እና ሃሳብ በሙሉ በቀጥታ ወደ ፍ/ቤት በአግባቡ ማቅረብ፤

7) ማንኛውም ባለጉዳይ ክርክሩን ወይም ጉዳዩን ለዳኛ ሲያቀርብ ዳኛን ፊት ለፊት እየተመለከተ መሆን አለበት

8) በችሎቱ ላይ የተነገሩት ጉዳዮች ትክክል መሆናቸው ወይም አለመሆናቸው በአይን ምልክት፣ በቅንድብ፣ በፊት ወይም በሌሎች አካል እንቅስቃሴ በመግለጽ ወይም ከዳኛው ወይም ከችሎት ዞር በማለት መናገር ከዳኛ ጋር መሟገት ክልክል ነው፤

9) በችሎቱ ላይ ተቃውሞውን፣ ክርክሩን እና ሁሉንም ሃሳብ ፍትህን፣ እውነታ እና አግባብነት ያላቸውን ማስረጃዎች ብቻ መሰረት በማድረግ ይግባኝ ማቅረብ፤

10) በችሎቱ ክርክር ላይ የዳኛውን ስም መጥራት ሳያስፈልግ እንደ "ክቡር ፍ/ቤት" ወይም "ክቡር ዳኛ" ወይም " ክብርት ዳኛ" በማለት መጥራት፤

11) የችሎቱን ስነ-ምግባር የማረጋገጥ ግዴታ በቀደምትነት የዳኛው ድርሻ ቢሆንም የችሎቱ ስነ-ስርዓት እንዳይጣስ የድርሻውን መወጣት፤

12) በተዘጋጀ ስፍራ ላይ ቆሞ ክርክርና አቤቱታ ማቅረብ

13) ባለጉዳዩ ችሎቱ ከመጀመሩ በፊት ምስክሮቹ መቅረባቸውን ማረጋገጥ አለበት

14) በክሳቸው ወይም በመልሳቸው ላይ በዘረዘሩት ምስክሮች ጋር በሚጣጣም መልኩ ማንነታቸውን እና አድራሻቸውን (የመታወቂያ ወረቀታቸውን ይዘው እንዲቀርቡ በማድረግ) በአግባቡ በማረጋገጥ አጣምሮ ማቅረብ፤

15) ማንኛውም በያዘው ጉዳይ ተከራካሪ የሆነ ሰው ምስክሮችን በአግባቡ ማናገር እና ክብራቸውን በመጠበቅ ጥያቄ ማቅረብ፤

16) ትዕዛዝ፣ ብይን ወይም ውሳኔ በሚነገርበት ጊዜ ወይም የተቃውሞውን ቃል ሳያሳይ በስነ-ስርዓት እና በጸጥታ እስከመጨረሻው በመስማት ቅሬታ ያለው ከሆነ ጉዳዩ በሚመለከተው አካል ይግባኝ ማቅረብ፤

17) በህክምና የተረጋገጠና በልዩ ሁኔታ በችሎቱ ዳኛ ካልተፈቀደ በስተቀር ማንኛውም የችሎት ባለጉዳይ የህግ ባለሙያዎችን ጨምሮ በችሎት አዳራሽ ውስጥ መመገብ ወይም መጠጣት ወይም ማስቲካ ወይም ከረሜላ ማኘክ የለበትም፡፡

18) በማንኛውም ሁኔታ በፍርድ ቤቶች ቅጥር ግቢም ሆነ በችሎት አዳራሽ ውስጥ ማንኝም ሰው ሲጋራ ማጨስ፣ ጫት መቃም የለበትም፡፡ 19) በመጠጥ ስካር ወይም በዕጽ ምርቃና መንፈስ ወደ ችሎት መግባት ፈጽሞ የተከለከለ ነው፡፡ ሳል ወይም ጉንፋን ያለው ባለጉዳይ ሁኔታውን ለችሎቱ በማሳወቅ በቅድሚያ እንዲስተናገድ ወይም ከችሎት ውጭ ሆኖ ተራውን እንዲጠብቅ ሊጠየቅ ይችላል፡፡

20) አስገዳጅ ሁኔታ ከሌለ በስተቀር ልጆችንና ሕፃናትን ወደ ችሎት ይዞ መግባት አይቻልም፡፡ ፍርድ ቤቱ በሚያዘጋጀው የልጆችና ሕፃናት ማቆያ ሥፍራ የችሎት ጉዳዩ እስኪጠናቀቅ እንዲቆዩ ይደረጋል፡፡

21) በፍርድ ቤቱ ቅጥር ግቢ፣ በችሎት፣ በዳኞች ጽ/ቤት አካባቢ ዳኞችን በድምጽ መረበሽ ፈጽሞ የተከለከለ ተግባር ነው፡፡

22) ተከራካሪ ወገኖች ሳይፈቀድላቸው መናገር በክርክር ጣልቃ መግባት አይችሉም

23) ዳኛ በሚናገርበት በማናቸውም ወቅት ጣልቃ በመግባት ማቋረጥ ፈጽሞ የተከለከለ ነው

24) ለችሎቱ ጉዳያቸውን ሲያስረዱ የቃላት አጠቃቀምን በመጠንቀቅ፤ ተገቢነት ወይም ግልጽነት የሌላቸውን ቃላት ከመጠቀም በመቆጠብ፣ በፍርድ ቤቱ የስራ ቋንቋ አቻ ቃላት ካጣ ችሎቱን ካላስፈቀደ በስተቀር ሌሎች ቋንቋዎች ቃላት መደባለቅ የተከለከለ ነው።

25) በማንኛውም ሁኔታ ጣትን ወደ ዳኛ፣ የችሎቱ ባለጉዳይ ወይም ታዳሚ ላይ እየቀሰሩ ማውራት፣ በክርክር ወቅት እጅን ኪስ ውስጥ አድርጎ ማውራት ወይም እጅን ማወናጨፍና መሰል ተገቢነት የሌላቸውን አካላዊ እንቅስቃሴዎች እያደረጉ ማውራት የተከለከ

26) ማንኛውም ተከራካሪ ክርከሩን ሲያቀርብ የሌላኛውን ወገን ሰብዕና በማዋረድ፣ በማስፈራራት ወይም በማሽማቀቅ ወይም በማሸሚጠጥ ሊሆን አይገባውም።

27) ተከራካሪ ወገኖች በችሎት ውስጥ በሚደረግ ክርክር ሃሳበቸውን በቀጥታ ለችሎቱ ከማቅረብ በቀር የጎንዮሽ ንግግር የተከለከለ ነው። 28) ከላይ የተዘረዘሩትና መሰል ተግባራትና የስነምግባር ጥሰቶች መፈፀም የተከለከለ ነው።

**20.** ከሬጅስትራር እና ከፍ/ቤቱ አስተዳደር ሰራተኞች የሚጠበቅ ስነ-ምግባር

1) ለችሎቱ በቂ ድጋፍ የሚሰጡ የአስተዳደር ሰራተኞች መመደብና በማንኛውም ሁኔታ ሲጓደል ችሎት ከመጀመሩ በፊት ማሟላት 2) በእለቱ የተቀጠሩ መዛግብትን ከቀጠሮ ቀን በፊት ለዳኛ አሟልቶ ማቅረብ

3) የችሎቱን ስራ ሳያደናቅፉ ወይም ሳያውኩ መስራት፤

4) እርስ በእርሳቸው ወይም ባለጉዳዮችን በማክበር በአግባቡ ማስተናገድ፤

5) በዳኛው የሚሰጠውን ትዕዛዝ ማክበር፣ መቀበል እና በተሰጠበት ቀን በስራ ላይ ማዋል፤

6) ለችሎቱ ስራ እጅግ አስፈላጊ ካልሆነ በስተቀር ክርክር እየተካሄደ ዳኛውን፣ ተከራካሪ ወገኖችን፣ ምስክሮቹን ወይም ከማንኛውም ሰው ጋር አለማውራት

7) የፍ/ቤቱን መዝገብ እና ሰነዶች በአግባቡ መያዝ፣ በወቅቱ ለችሎቱ ማቅረብ ፤

8) የመዝገቡን ሚስጥር መጠበቅ ማንኛውንም አይነት ማስረጃ ወይም ጽሁፍ ከችሎቱ ፍቃድ እና እውቅና ውጪ ከመዝገቡ ጋር እንደተያያዘ ማረጋገጥ፤

**21.** ከቋንቋ አስተርጓሚ የሚጠበቅ ስነ-ምግባር

1) ቋንቋ የመተርጎም አገልግሎት በአግባቡ ማካሄድ፤ 2) ባለጉዳዮችን ማክበር እና በአግባቡ ማስተናገድ፤ 3) ያለአድልኦ ትክክለኛውን ትርጓሜ ማስተላለፍ፤

4) የዳኛውን ትዕዛዝ ማክበር፣ መቀበል እና መተግበር፤

5) በእውነት ለመተርጎም በገባው ቃለ መሀላ መሰረት መተርጎም፤

6) ሌሎች ፍርድ ቤቱ በሚያወጣው መመሪያ መሰረት የተገለፁትን ተግባራት መፈፀም አለበት

**22.** ከችሎት አስከባሪ የሚጠበቅ ስነ-ምግባር

1 ማንኛውም ሰው የችሎት ስርዓት እንዲያከብር ማድረግ የችሎት ስርዓት ተጥሶ ሲገኝ ለችሎቱ ዳኛ የማሳወቅ፤

2 አቃቤ ህጎችን እና የመከላከያ ጠበቃን ሳይጨምር ወደ ችሎቱ የገቡትን ሰዎች በሙሉ በመፈተሽ ማስገባት፤

3 በዳኛው የሚሰጠውን ትዕዛዝ ማክበር፣ መቀበል እና በአግባቡ መተግበር፤

4 ባለጉዳዮችን፣ ምስክሮችን፣ ተከራካሪ ወገኖችን እና ችሎቱን የሚከታተሉ ማናቸውንም ሰዎች ማክበር፤

5 የችሎቱ ክርክር በመካሄድ ላይ ሳለ በችሎቱ ከታዘዘ እንጂ ጣልቃ በመግባት መናገር ወይም በመንቀሳቀስ የችሎቱ ስራ እንዳይደናቀፍ ወይም እንዳይታወክ ማድረግ፤

6 ለችሎቱ ስራ አስፈላጊ ከሆነ እንጂ ከዳኞች፣ ከምስክሮች፣ ከባለጉዳዩ እና ችሎቱን ከሚከታተሉ ከማንኛውም ሰዎች ጋር አለማውራት፤

7 ትዕዛዝ እና ውሳኔ በሚነበብበት ጊዜ በአግባቡ በመስማት እንዲተገበር የበኩላቸውን ድርሻ ማበርከት፤

8 የችሎቱን ፀጥታና ድህንነት ማረጋገጥ፤

ክፍል ሶስት

ከችሎቱ ውጪና በችሎት አካባቢ የተከለከሉ ድርጊቶች

**23.** በችሎት የተከለከሉ ድርጊቶች

ማንኛውም ሰው በችሎቱ ላይ የሚከተሉትን ድርጊቶች መፈጸም ክልክል ነው፡፡

1) ለችሎቱ ስራ ሳያስፈልግ ማንሾካሾክ ወይም ድምጽ ከፍ በማድረግ መናገር ወይም መንጫጫት ወይም ጎኑ ካለው ወይም ከሌላ ሰው ጋር ማውራት ወይም መነጋገር፤

2) በሞባይል መነጋገር

3) ጋዜጣ እና ማንኛውንም ሌሎች ጽሁፎችን ማንበብ፣

4) ሲጋራ ማጨስ፣ ቃጠሎ የሚፈጥሩ መሳሪያዎችን ይዞ መግባት፣

5) በድምጽ፣ በምልክት ወይም በማንኛውም ሁኔታ ችሎቱን ማወክ ወይም ለክርክሩ አስፈላጊ ያልሆነውን ድርጊት ወይም ንግግር ማድረግ፣ የሰውን ስሜት የሚስብ/የሚነካ ተግባር መፈፀም፣

6) መጠጣት፣ መመገብ፣ ጫት መቃም፣ ማስቲካ ማኘክ፣ መተኛት፣

7) የዳኛ ፈቃድ ሳይኖር ጠበቃ ተጠርጣሪውን ወይም ተከሳሹን ማነጋገር፣

8) የጦር መሳሪያ፣ ዱላ ወይም ስለታማ የሆኑ መሳሪያዎችን መያዝ ሆኖም የችሎቱን ስነ ስርዓት አስከባሪ፣ ተጠርጣሪውን ወይም ታሳሪውን ይዞ ወደ ችሎቱ የመጣውን ፖሊስ ወይም በልዩ ችግር ምርኩዝ ዱላ ይዞ የሚንቀሳቀስን አይጨምርም፣

9) ስልጣን ካለው አካል ፍቃድ ሳኖረው በሞባይል፣ በካሜራ ወይም በቪዲዮ ፎቶ ማንሳት ወይም ድምጽ መቅዳት፣

10) እንደ ሻንጣ፣ፌስታል እና ትላልቅ በርሳዎች ወይም ለችሎቱ ስነ-ስርዓት የማይመች ድምጽ መፍጠር የሚችሉ ማንኛውንም እቃዎች ይዞ ወደ ችሎቱ መግባት፣

11) በማንኛውም መልኩ የችሎቱን ሰላምና ፀጥታ ማወክ

**24.** የመገናኛ ብዙኃን ችሎት አጠቃቀም

1. ችሎቱ ከሚካሄድበት ዕለት 24 ሠዓት አስቀድሞ የችሎቱ ዳኛ በግልጽ ካልፈቀዱ በቀር ጋዜጠኞች የችሎት ሂደትን በምስልና በድምጽ ሊቀዱ አይችሉም፡፡

2. በልዩ ሁኔታ ሲፈቀድ የችሎት ሂደትን የመገናኛ ብዙኃን ተቋማት በቀጥታ ሥርጭት ሊያስተላልፉ ይችላሉ።

3. ችሎት ከተጀመረ በኋላ ጋዜጠኞች ወይም የካሜራ ባለሙያዎች ችሎት ውስጥ እንቅስቃሴ በማድረግ የችሎቱን ሂደት ማስተጓጎል አይችሉም።

4. የችሎቱን ሥፋት ከግምት ውስጥ በማስገባት ዳኞች የጋዜጠኞችንና የመቅጃ መሣሪያዎችን ቁጥር ሊወስኑ ይችላሉ።

5. የሚዲያ ተቋማቱ የሚጠቀሙባቸው መሣሪያዎች በድምጽ ወይም በብርሃን የችሎቱን አትኩሮት የሚረብሹ መሆን የለባቸውም።

6. የችሎት ሂደትን ለመዘገብ የሚፈልጉ የሚዲያ ተቋማት ቢያንስ ችሎቱ ከመሰየሙ ከ15 ደቂቃ በፊት የተፈቀደላቸውን ቦታ በመያዝ የቀረፃ ዝግጅታቸውን ማጠናቀቅ አለባቸው። ሆኖም ችሎቱ ከተሠየመ በኋላ ምንም ዓይነት እንቅስቃሴ ማድረግ አይፈቀድም።

**25.** የችሎት ደህንነትን ስለማስጠበቅ

1. ከዳኞች በቀር ማንኛውም ወደ ፍርድ ቤት ወይም ችሎት አዳራሽ የሚገባ ማንኛውም ባለጉዳይ በደህንነት ፍተሻ ሥር የማለፍ ግዴታ አለበት።

2. ማንኛውም ወደ ችሎት የሚገባ ባለጉዳይ የህግ ባለሙያዎችን ጨምሮ ዱላ፣ ስለት ወይም የጦር መሣሪያ በመያዝ ወደ ችሎት ወይም ፍርድ ቤት ግቢ መግባት አይችልም።

3. ከላይ የተመለከተው ቢኖርም የፖሊስና ማረሚያ ቤት አባላት እስረኞችን ለማጀብ የተሰጣቸውን ሕጋዊ መሣሪያ እንደያዙ ፍርድ ቤት ግቢ መግባት አይከለከሉም። ሆኖም እነዚህን መሣሪያዎች ይዘው ወደ ችሎት አዳራሽ መግባት አይፈቀድላቸውም።

26 የችሎት ማጠናቀቂያ ስርዓት

1) ዳኞች የችሎት ስራውን ሲያጠናቅቁ የችሎት ሰብሳቢው በችሎት ውስጥ የተገኙትን ሰዎች በማመስገን ጠረጴዛውን በችሎት መዶሻ በመምታት ስለችሎቱ መጠናቀቅ ማሳወቅ አለበት፡
2) ችሎት ሲጠናቀቅ የችሎት ስርዓት አስከባሪው ወይም ፖሊስ ለዳኞች የሰላምታ ምልክት በማሳየት ዳኞችን እና በችሎት ላይ የተገኙ ሰዎችን መሸኘት አለበት።

ክፍል አራት

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

27 ችሎቱ የሚወስደው እርምጃዎች

1) የእርምጃ እና የቅጣት አላማ ሰው በፈጸመው ጥፋት ተፀፅቶ እራሱን ማስተካከል እንዲችል ማድረግ፣ ሌሎች ሰዎችም እንዲማሩበት ማድረግ እና የችሎቱ ክብር እንዲጠበቅ ማድረግ ነው፣
2) የችሎቱን ስነ ስርዓት በጣሰው በማንኛውም ሰው ላይ የችሎቱ ዳኛ የድርጊቱን አፈፃፀም እና ከተፈጸመ

ሀ. ማስጠንቀቂያ መስጠት፣

ለ. ለተወሰነ ጊዜ ወደ ችሎቱ እንዳይገባ መከልከል፣

ሐ. ከችሎቱ ክፍል እንዲወጣ ማድረግ ወይም

መ. በወንጀል እና በፍትሓብሔር ህግ መሰረት የችሎቱን ስርዓት በመጣስ፣ በማወክ ወይም በማደናቀፍ ወንጀል ወዲያውኑ

ፍርድ መስጠትና ቅጣት መወሰን አለበት።

3) ዳኛው የዚህን መመሪያ ድንጋጌዎች ከጣሰ በዳኞች የስነምግባር ደንብ ቁ. --/2013 መሰረት ተጠያቂ ይሆናል። ***29*** መመሪያውን ስለማሻሻል

የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይህንን

መመሪያ ሊያሻሻል ይችላል፡፡ **30** የተሻሩና

ተፈፃሚነት የማይኖራቸው ህጎች

ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረን ማንኛውም መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሰራር በዚህ መመሪያ የተሸፈኑ ጉዳዮችን በተመለከተ ተፈፃሚነት የለውም፡፡

31 መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከ----- ቀን 2013 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

ወ/ሮ መዓዛ አሸናፊ

የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ፕሬዝዳንት

አዲስ አበባ